የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር

መተዳደሪያ ደንብ (የተሻሻለ)

ታህሳስ 2013፣ አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር

መተዳደሪያ ደንብ (የተሻሻለ)

አጠቃላይ ውሳኔ

እኛ የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር አባላት ቀጥሎ በተዘረዘረው ድንጋጌዎች ለመተዳደር በ1998 ዓ.ም ያጸደቅነውን የመተዳደሪያ ደንብ በሙሉ ፈቃደኝነት በመስማማት በማሻሻል ይህ መተዳደሪያ ደንብ ማህበሩ ለስራው አመራር የሚጠቀምበት ህጋዊ ሰነድ እንዲሆን በሙሉ ድምጽ አጽድቀነዋል። በተጨማሪም ማህበሩ በተጠቀሰው ደንብ ብቻ ሳይወሰን የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክርቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995፣ የዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራት እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ድጋፍ አሰጣጥና ክትትል መመሪያ ቁጥር 2/2007 በማህበሩ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እናረጋግጣለን።

አንቀጽ 1

መቋቋም

ማህበሩ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 404 እና በማህበሮች ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/1959 እንዲሁም የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 መሰረት የካቲት 9 ቀን 1998 ዓ.ም ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል።

አንቀፅ 2

ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ማህበር የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ‹‹ማህበር›› ተብሎ ይጠቀሳል።

አንቀጽ 3

ትርጓሜ

‹‹የዘርፍ ማኅበር›› ማለት አምራች ድርጅቶች በየተሰማሩበት መስክ የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 404 መሰረት ያቋቋሙት ህጋዊ ማህበር ነው።

አንቀጽ አራት (4)

አርማና ማህተም

ማህበሩ ዓላማውንና ተግባሩን የሚያመለክት አርማና ማህተም ይኖረዋል።

የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር 020/4/013 ECPMA Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

አንቀጽ አምስት (5)

የማህበሩ አድራሻ

የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር አዲስ ስልክ ቁጥር 0115582039 የሚገኝ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎችም ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ሊከፍት ይችላል።

አንቀጽ ስድስት (6)

የማህበሩ ዓላማዎች

ማህበሩ የተቋቋመው ለሚከተሉት ዓላማዎች ነው፡-

6.1. ዘርፉ የሚደራጅበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣

6.2. የምርቶች የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል ለአባላቱ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣

6.3. የምርቶችን የደረጃና ጥራት ማረጋገጫና ከአካባቢ ብክላ የጸዱ የአመራረትና የአካባቢ ንጽህና ቁጥጥርን በሚመለከቱ መስኮች የምክርና የድጋፍ አገልግሎትን መስጠት

6.4. የምርት መረጃዎችን ማጠናከርና ማሰራጨት፣

6.5. ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ዘርፍ ማህበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለአባላቱ የሚጠቅም የልምድና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣

6.6. በዘርፉ ለተሰማሩ አምራቾች በጋራ የማምረትና የግብይት አቅማቸውን ለማሳደግ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ መምከር እና መተግበር፣

6.7. አባላት በዘርፉ ያካበቱትን እውቀትና ልምድ አስመልክቶ መረጃዎችን የሚለዋወጡበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

6.8. አባላት ከማህበሩ ጋር የተያያዘ ትምህርትና አዳዲስ ሀሳቦችን ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

6.9. ማህበሩን በሚመለከት አገር አቀፍ ጉባኤዎችን፣ ሴሚናሮችን እንዲሁም ኤግዚቢሽኖችን ማዘጋጀትና ማበረታታት፣

6.10. አባላት ዕውቀታቸውን፣ ሀብታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣

6.11. አባላት ጥቅማቸውን በጋራ ለማስጠበቅ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

6.12. ማህበሩ ዘርፉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከመንግስት ጋር የጋራ ውይይት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

6.13. ዘርፉን በሚመለከት የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን ማጥናትና የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመንግስት ማቅረብና ውሳኔ እንዲሰጥባቸውም አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ፣

የኢትዮጵያ ኬሚካል ምርቶች አምራቾች ማህበር
02/04/2013
ECPMA
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

6.14. ትክክለኛ ሀቀኛ የንግድ ስነ ምግባር እንዲኖር በማህበሩ አባላት መካከል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ልምድ እንዲመሰረት ጥረት ማድረግ፣

6.15. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች እና ከንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ጋር በመረጃ ልውውጥ፣ በቴክኒካል እገዛዎችና በመሳሰሉት በትብብር መስራት።

አንቀፅ ሰባት (7)

የማህበሩ የአባልነት መስፈርት

ማህበሩ መስራች አባላትና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለአባልነት ብቁ የሆኑ መደበኛ አባላት ይኖሩታል። አባል የሚሆነው በፈቃደኝነት ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሲያሟሉ ነው።

7.1. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ፣
7.2. ህጋዊ ሰውነት ወይም ፈቃድ ያለው፣
7.3. መመዝገቢያና መዋጮ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ፣
7.4. ለማህበሩ የጉልበትና የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ፣
7.5. ንግድና ኢንዱስትሪ ባወጣውና በሚያወጣው ደንቦች የታቀፈ።

አንቀጽ ስምንት (8)

የክብር አባላት

8.1. የማህበሩ አባላት ሳይሆኑ ለማህበሩ ዓላማዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ወይም ማህበሩ በሚንቀሳቀስበት ጉዳይ ዙሪያ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች/ ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የማህበሩ የክብር አባላት ሊሆኑ ይችላሉ።

8.2. የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ በሚካሄዱ ምርጫዎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብት የላቸውም።

8.3. የክብር አባላት በራሳቸው ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮ ወይም ሌላ መዋጮ እንዲከፍሉ አይገደዱም።

አንቀጽ ዘጠኝ (9)

ለአባልነት ስለማመልከት

9.1. ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራና አባል ለመሆን የሚፈልግ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥያቄውን በጽሁፍ በማድረግ ለማህበሩ ዋና ፀሐፊ ያቀርባል።

9.2. ዋና ፀሐፊውም የአባልነት ማመልከቻ እንደደረሰው የውሳኔ ሃሳብ እንዲሰጥበት ጥያቄ ለስራ አስፈጻሚ ኬሚቴ አባላት ያቀርባል።

9.3. የአባልነት ጥያቄውም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ አመልካቹ በማህበሩ አባላት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

9.4. በአባልነት ለተመዘገቡ የማህበሩ አባላት መታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል።

አንቀጽ አስር (10)

የአባላት መብት

10.1. ሁሉም አባላት እኩል መብት አላቸው።
10.2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው።

የኢትዮጵያ ኬሚካል ምርቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር
020/4/013
ECPMA
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

10.3. አንድ አባል የሚጠበቅበትን መዋጮ ካልከፈለ ወይም የሚጠበቅበትን አገልግሎት ካልሰጠ በሙሉ አይሰራበትም።

10.4. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል።

10.5. የመምረጥ፣ የመመረጥ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት አለው።

10.6. በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው።

10.7. ማህበሩ የሚያስገኛቸውን ማንኛውንም ጥቅሞች እኩል የማግኘት መብት አለው።

10.8. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በቦርዱ የመሰማት መብት አለው።

አንቀፅ አስራ አንድ (11)

የአባላት ግዴታ

ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል የሆነ ሰው ወይም ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል።

11.1. ማንኛውም አባል የአባልነት ክፍያ በወቅቱ የመክፈል ግደታ አለበት።

11.2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ በፊት የሚፈለግበት እዳ ካለ የመክፈል ግደታ አለበት።

11.3. የማህበሩን ዓላማዎች፣መተዳደሪያ ደንብ፣በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና በማህበሩ ሌሎች አካላት የሚተላፉ ሕጋዊ ውሳኔዎችን ማክበር።

11.4. የአጠቃላይ ጉባኤውን ውሳኔዎች ማክበር እና በተጠየቀ ጊዜም ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር አለበት።

11.5. በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ መገኘት።

11.6. አባላት የማህበሩን ንብረቶች የመንከባከብና የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።

አንቀጽ አስራ ሁለት (12)

አባልነት የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

12.1. አንድ አባል በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተገለጸው መሰረት ወይም ሌላ አጥጋቢ ምክንያት ሲኖር ከማህበሩ እንዲወጣ ጠቅላላ ጉባኤው ሊወስን ይችላል።

12.2. አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ የሚቋረጠው።

12.2.1. ጠቅላላ ጉባኤው አባሉ የማህበሩን ክብር ወይም መልካም ስም ወይም ህልውናውን የሚጎዳ ድርጊት መፈፀሙን የሚያሳይ መረጃ በማግኘት ምክንያት አባልነቱን ለማቋረጥ ሲወስን።

12.2.2. ለማህበሩ ዓላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚጠበቀውን ተሳትፎ ካላደረገ።

12.2.3. መዋጮውን ለ 2 (ሁለት) ተከታታይ ጊዜ ሳይከፍል ከቀረና በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ ሲሰረዝ።

12.2.4. በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ ማመልከቻ ሲያቀርብ።

12.2.5. አባሉ ሲሞት፣ ሲከስር ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም በሕግ ክልከላ ሲጣልበት።

12.2.6. የድርጅቱ ህልውና በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ ነው።

አንቀጽ አስራ ሶስት (13)
የማህበሩ መዋቅር

ማህበሩ በሚመለከተው መልኩ የተዋቀረ ነው፡፡



አንቀጽ አስራ አራት (14)
የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ መተዳደሪያና መመስረቻ ጹሁፍ አንቀፅ 7 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላትን የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

14.1. ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡

14.2. ከማህበሩ አባላት መካከል የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን (ሊቀ መንበሩን፣ ም/ሊቀ መንበሩን፣ ፀሐፊውን፣ ሂሳብ ሹሙን እና አባላቶችን) ይመርጣል፤አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያሰናብታል፡፡

14.3. የማህበሩን የፖሊሲ፣የመርሃ-ግብርና የአተገባበር ስልት አቅጣጫዎችን ይወስናል፡፡

14.4. የአባላትን መዋጮና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ይወስናል፡፡

14.5. የማህበሩን አመታዊ እቅድና በጀት ያፀድቃል፡፡

14.6. የቦርዱን አመታዊ ሪፖርትና የኦዲት ሪፖርት ይገመግማል፣ያፀድቃል፡፡

14.7. በአባልነት መቋረጥ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

14.8. የማህበሩ አባል ለመሆን የቀረበ ጥያቄን ይመረምራል ያጸድቃል፡፡

14.9. ሊቀመንበሩ የሚያቀርበውን አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማዳመጥ ማህበሩ የተቋቋመበት ዓላማና የተነደፉ መርሃ ግብሮች ተግባራዊ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፡

14.10. የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል።

14.11. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መደበኛና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ያፈርሳል።

14.12. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመመስረቻ ሰነዱን ያሻሽላል።

14.13. እንደአስፈላጊነቱ የማኀበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚለወጥበት እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚከፈቱበተ ሁኔታ ላይ ይወስናል።

14.14. እንደአስፈላጊነቱ የማኀበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል።

14.15. በማህበሩ መፍረስ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

14.16. ለሌላ የማህበሩ አመራር አካል ያልተሰጡ ጉዳዮችን ይወስናል።

14.17. ጠቅላላ ጉበኤው ጉዳዩ ከሌሎች ህጋጋት ጋር ግጭት አስካልፈጠረ ድረስ በመመስረቻ ፁሁፉ ላይ የመጨረሻ ትርጉም ይሰጣል።

አንቀጽ አስራ አምስት (15)

የጠቅላላ ጉባኤው የስብሰባ፣ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

15.1. የጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ ሆኖ እጅግ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ አስቸኳይ ስብሰባ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት ይካሄዳል።

15.2. ከማህበሩ አባላት 10 % በላይ በሚሆኑ አባላት ጥያቄ የጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ በሊቀመንበሩ በኩል ሊጠራ ይችላል።

15.3. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ሶስት የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ።

15.4. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል።

15.5. የማህበሩ መደበኛ አባላት 50 % በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። ይህ ሳይሟላ ቀር[illegible] ሁለተኛ ጥሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በአግባቡ ለአባላት መድረሱ ሲረጋገጥ በተገኙት አባላት በጥሪው ላይ በተገለጸው አጀንዳ ላይ ብቻ ሊሰጥ ይችላል።

15.6. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስበሰባው ላይ በተገኙ አባላት ድምጽ ብልጫ ሆኖ እኩል ድምጽ ሲኖር ሊቀመንበሩ የደገፈው ውሳኔ ይሆናል፡፡

15.7. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤው ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ሊቀመንበር /ፀሃፊ በፁሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ አስራ ስድስት (16)

የማህበሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

16.1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚያደርገው ምርጫ የሚመረጠው የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቁጥር ከ5 እስከ 7 የሚሆኑ ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባዔው ነው፡፡

- ✓ ሊቀመንበር
- ✓ ምክትል ሊቀመንበር
- ✓ ፀሐፊ
- ✓ ሂሳብ ሹም እና
- ✓ አባል ናቸው፡፡

16.2. የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፡፡

አንቀጽ አስራ ሰባት (17)

የማህበሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

17.1. የማህበሩን ስራ አስኪያጅ ይቀጥራል፤አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ያሰናብታል፡፡

17.2. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

17.3. በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡ ውሳኔዎችና የሚወጡ ዕቅዶችን በስራ አስኪያጁ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ይቆጣጠራል፤ይከታተላል፡፡

17.4. ለማህበሩ ፕሮግራም አስፈላጊው ሀብት ስለመኖሩ ያረጋግጣል፡፡

17.5. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ መርሀ ግብርና የአጭር፤ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

17.6. የማህበሩን ዓላማዎች ለማስፈጸም የገቢ ምንጮች፤ የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይፈልጋል።

17.7. የማህበሩን ፖሊሲ በማመንጨት ያቀርባል።

17.8. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትን ደንብ ያወጣል፤ ዝውውር፣ዕድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል።

17.9. በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል።

17.10. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል።

17.11. የአባልነት ግዴታዎችን ያልተወጡ አባላት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

17.12. የራሱን የአሰራር ስነ ስርዓት ያወጣል።

17.13. በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

17.14. የማህበሩን መደበኛ አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል።

አንቀጽ አስራ ስምንት (18)

የማህበሩ ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

18.1. ማህበሩን በሊቀመንበርነት ይመራል።

18.2. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን በሊቀመንበርነት ይመራል።

18.3. የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።

18.4. የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ከስራ ሲለቅ እኪቀጠር/ እኪሾም ድረስ ስራ አስኪያጁን ተክቶ ይሰራል።

18.5. ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል።

18.6. በማህበሩ ስም የተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቼኮችንና የወጪ ሰነዶች ከስራ አስኪያጁ ወይም በአማራጭ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል።

18.7. ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚያወጣቸውን የማህበሩን ፖሊሲዎች፤ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያፀድቃል።

18.8. ጠቅላላ ጉባኤው እና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለስራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ይሰጣል።

18.9. ሊቀመንበሩ ሀሳቡን ለማጽደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም።

18.10. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔን በማይቃረን ሁኔታ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

የኢትዮጵያ የኬሚካል ምርቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር
020/4/013
ECPMA
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ (19)

የማህበሩ ምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

19.1. ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

19.2. ሊቀመንበሩ ወይም ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ስራ ያከናውናል፡፡

19.3. የማህበሩ ምክትል ሊቀመንበር ተጠሪነቱ ለማህበሩ ሊቀመንበር ነው፡፡

አንቀጽ ሃያ (20)

የቦርዱ ፀኃፊ ተግባርና ኃላፊነት

20.1. የጠቅላላ ጉባኤውንና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከሊቀመንበሩ ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፡፡

20.2. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

20.3. የጉባኤውን ሰነድ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

20.4. ከሂሳብ ሰነዶች ውጭ ያሉትን ማንኛውንም የማህበሩን መዛግብትና ሰነዶችን ይጠብቃል፡፡

20.5. ተጠሪነቱ ለሊቀመንበሩ ይሆናል፡፡

አንቀጽ ሃያ አንድ (21)

የኦዲተር ተግባርና ኃላፊነት

የማህበሩ ኦዲተር ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ስልጣን ይኖሩታል፤

21.1. የማህበሩን ገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፡፡

21.2. የማህሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያና በመመስረቻ ፁሁፍ ስለመከናወኑ ያረጋግጣል፡፡

21.3. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፡፡

አንቀጽ ሃያ ሁለት (22)

የማህበሩ ሂሳብ ሹም ኃላፊነትና ተግባር

የማህበሩ ሂሳብ ሹም ተጠሪነቱ ለስራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

22.1. የማህሩን ሂሳብ ገቢና ወጪ ይቆጣጠራል፤በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያርጋል፡፡

22.2. የማህበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በትክክለኛው የሂሳብ አሰራርና ደንብ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

22.3. የማህበሩን የባንክ ሂሳብና ቼክ ወይም ሃዋላ ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ጊዜ ከስራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፈርመው ያንቀሳቅሳል፡፡

22.4. የማህበሩ ሂሳብ መዛግብትና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

22.5. የሂሳብ መዝገብ፤ ገቢና ወጪ፤ሃብትና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

20/4/013
ECPMA
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

22.6. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ ሃያ ሶስት (23)

የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ኃላፊነትና ተግባር

የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

23.1. በማናቸውም አካል ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፤የማህሩን ስራ በተመለከተ ማናቸውንም ጉዳዮች ይፈፅማል ውክልና ይሰጣል፤በማህበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል፤በማህሩ ስም ውል ይዋዋላል፡፡

23.2. በማህበሩ ስም የሚከፈተውን ሂሳብና ቼክ ወይም ሃዋላ፤ከሊቀመንበሩ ጋር እንዲሁም በአማራጭ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጣምራ ያንቀሳቅሳል፡፡

23.3. በስራ አስፈጻሚውና በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

23.4. የማህበሩን የሶስት ወር፤የስድስት ወር እና የዓመት የስራና የፋይናንስ ሪፖርት እያዘጋጀ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

23.5. የማህበሩን ፖሊሲና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

23.6. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚያወጣቸው አስተዳደራዊ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ያሰናብታል፡፡

23.7. ከሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ ውጪ ያሉትን የስራ መደቦችን በማዘጋጀት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

23.8. የጠቅላላ ጉባኤውን እና የቦርዱን ዕቅዶች፣ፖሊሲዎች እና የማስፈፀሚያ ስልቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዕቅዶችና ስልቶች ይነድፋል፡፡

23.9. የጠቅላላ ጉባኤውን ውሳኔዎች ይተገብራል፣

23.10. በመንግስታዊ አካላት፣ በፍርድ ቤት፣ በመዘጋጃ ቤትና ሌሎች የአካባቢ ወይም ብሔራዊ የመስተዳድር አካላት፣በግል ተቋማት፣በሕግ የሰውነት መብት በተሰጣቸው አካላት፣በግለሰቦችና በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፣

23.11. በማህበሩ ስም ውሎችን ይዋዋላል፣ ይፈርማል፣ ይፈጽማል፣ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስራ አስኪያጁ የሚዋዋላቸውና የሚፈርማቸውን ውሎች በመጠን ወይም በዓይነት ሊወስን ይችላል፡

23.12. ክሶችንና ክርክሮችን ይመሰርታል፣ይከሳል፣ይካሰሳል ይከላከላል፣በማህበሩ ስም አገልግሎቶችን ይቀበላል፡፡

የኢትዮጵያ ኬሚካል ውጤቶች አምራቾች ማህበር
ECPMA
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

23.13. የጠቅላላ ጉባኤውን፣ የቦርዱንና ሌሎች የማህበሩን ስብሰባዎች ሂደት ይመዘግባል፣ የሂሳብ መዝገብን ጨምሮ የማህበሩን እንቅስቃሴዎች ይመዘግባል፡፡

23.14. በተጠየቀ ጊዜ የሂሳብ መዝገብን ጨምሮ የማህበሩን መዝገቦች ለኦዲተሩ ያቀርባል፡፡

23.15. ለአባላት ማሳወቅና መጥሪያ መላክን ጨምሮ ለጠቅላላ ጉባኤና ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል፡፡

23.16. ለስራ አስኪያጅ የሚፈፀሙ ክፍያና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስቀርቦ ያስወስናል፡፡

23.17. ስራ አስኪያጅ በሕግ፣ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ፣ በጠቅላላ ጉባኤውና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች የተጣሉበትን ኃላፊነቶች የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡ በዚህም ከአንድ ወኪል የሚጠበቀውን ጥንቃቄ ማድረግና በተለይም በአጠቃላይ ሥራ አመራር አስፈላጊውን ጥንቃቄና ትጋት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ ሃያ አራት (24)

የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ሃላፊነት

ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለማህበሩ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

24.1. የማህበሩን ገንዘብ በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፡፡

24.2. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፤ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

24.3. ለስራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥንቃቄ ወጪዎች የሚሆን ከብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፡፡

24.4. ከሂሳብ ሹሙ ጋር የገቢና የወጪ ሂሳብ በየወሩ ያመሳክራል፡፡

24.5. የማህበሩን ቼክ ይይዛል፡፡

24.6. በጣምራ ፊርማ በሊቀመንበሩ እና በስራ አስኪያጁ ወይም ሊቀመንበሩ በማይኖሩበት ጊዜ በሂሳብ ሹሙ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ ሃያ አምስት (25)

የማህበሩ ንብረትና የገንዘብ አስተዳደር ኃላፊነት

25.1. ማህበሩ በስሙ የባንክ ሂሳብ ይኖረዋል፡፡ ሂሳቡ የሚንቀሳቀሰው በማህበሩ ሊቀመንበር ሊቀመንበሩ በማይኖሩበት ጊዜ በሂሳብ ሹሙ እና በስራ አስኪያጁ ሲሆን ከእነዚህ ከሶስቱ በሁለቱ ፊርማ ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ የስራ አስኪያጁ ቋሚ ሲሆን በሂሳብ ሹሙ ፊርማ ተጨማሪነት ሂሳቡ ሊንቀሳቀስ ይችላል፡፡

25.2. በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ ሊቀመንበሩ፣

ECPMA
020/4/013
Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

ሀ. የንብረቶችና ዕዳዎች ግምት ዝርዝር መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

ለ. ስለ ሂሳብ ሚዛንና ባለፈው ዓመት ስለነበረው የማህበሩ ሁኔታና አሰራር ሪፖርት ያዘጋጃል፣

ሐ. የማህበሩን የሂሳብ መዝገብ ከዋና መስሪያ ቤት ሳይወጣ በጥንቃቄ ተጠብቆ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

25.3. ማህበሩ የሚያገኛቸው ገቢዎች በሙሉ ለማህበሩ ዓላማ ማስፈጸሚያ ብቻ ይውላሉ።

25.4. ማህበሩ ትክክለኛውን የሂሳብ ዝርዝር የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ይኖረዋል።

25.5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 27.1- 27.3. የተገለጹት እንደተጠበቀ ሆኖ የማሕበሩ ገንዘብ ገንዘብ በጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅ የፋይናንስ ደንብ መሰረት የሚተዳደር ይሆናል።

አንቀጽ ሃያ ስድስት (26)

የማህበሩ የገቢ ምንጭ

የማህበሩ ዋና ገቢ ምንጭ የአባላት ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ

- ✓ ከገቢ ማስገኛ ስራዎች፣
- ✓ ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

አንቀጽ ሃያ ሰባት (27)

የአባላት መመዝገቢያና ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ

የማህበሩ መሰረታዊ የገቢ ምንጭ የማህበርተኞቹ መዋጮ በመሆኑና ማህበሩም ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችለው ገቢው ሲጠናከር በመሆኑ አባላት የሚከተሉትን መዋጮ ያዋጣሉ።

27.1. እያንዳንዱ አባል ለመመዝገቢያ ብር 5000 (አምስት ሺ) ይከፍላል።

27.2. ዓመታዊ መዋጮ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ. ብር) ይሆናል

27.3. በየዓመቱ የሚከፈለው ዓመታዊ የአባልነት ክፍያ ከሃምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ቀን ይሆናል፤ በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ክፍያውን የማይፈፅም አባል ብር 2000 (ሁለት ሺ.) መቀጮ ይጣልበታል።

27.4. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን የገንዘብ ቅጣት ያልከፈለ አባል እዳውን ከፍሎ እስኪያጠናቅቅ ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው አባሉን ድምፅ የመስጠት ወይም ሌላ መብት ሊገድብ ይችላል።

27.5. ለአዲስ አባልነት የሚከፈል ክፍያ ለማንኛውም የበጀት ዓመቱ ጊዜ ውስጥ ቢከፈል የሚያገለግለው ለቀረው የበጀት ዓመት ብቻ ነው። የአባልነት መዋጮ አይሸራረፍም።

አንቀጽ ሃያ ስምንት (28)

የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላው ጉባኤው ¼ኛው ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል።

ECPMA
020/4/013

28.1. የዚህ መተዳዳሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ ወይም ምክትል ሰብሳቢ የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

28.2. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳብ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ¾ኛው ድምፅ ሲያገኝ ነው፡፡

አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ (29)

ስለ ማህበሩ መዋሃድና መለወጥ

29.1. ማህበሩ ወደ ተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው ፣ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ሌላ አይነት ማህበር የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛው ድምፅ ሲወሰን ነው፡፡

29.2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማህበር ጋር የሚደረገው ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ፣ፀሃፊና የማህበሩ ፕሬዚዳንት ማካተት ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ (30)

ስለ ማህበሩ መፍረስ

30.1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡

30.2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበር ሊቀመንበር የንብረት ቆጠራ (invoice) ሰርቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲያቀርብ፡፡

30.3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የንግድ ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ያለው የመንግስት አካል ሊወስን ይችላል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አንድ (31)

የበጀት ዓመት

የማህበሩ የበጀት አመት በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል

አንቀጽ ሰላሳ ሁለት (32)

የመተዳደርያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ተቀባይነት ካገኘና በሚፈቅድለት የመንግስት አካል ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ የኬሚካል ምርቶች አምራቾች የዘርፍ ማህበር 020/4/013 ECPMA Ethiopian Chemical Products Manufacturers Association

የማህበሩ ስራ አስፈጻሚ አባላት ስም	ፊርማ
1. [illegible]	[signature]
2. [illegible]	[signature]
3. [illegible]	[signature]
4. [illegible]	[signature]
5. [illegible]	[signature]
6. [illegible]	[signature]
7. [illegible]	[signature]

የኢትዮጵያ የኬ... አምራቾች የዘርፍ ማህበር
020/4/013
ECPMA
Ethiopian Chemical Prod...
Manufacturers Associa...